የአዲስ አበባ ሜዲካል እና ቢዝነስ ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ

የጉዞ መዝሙር ጥራዝ

አጫጭር መዘሙር

1. ተናገሩ 2
2. ኩሎዘፈቀደ 2
3. ኖላዊ ትጉህ 2
4. ንሴብሖ. 2
5. ኢትዮጵያታበጽህእደዊሃ 2
6. ለጌታዬለእግዚአብሄር 2
7. ስብሃትለአግዚአብሄርበሰማያት 2
8. እንተበምድር 2
9. በምድራዊሕይወት 2
10. ኢያቄምወሐና 2
11. በመኑ 2
12. እመቤታችን ማርያም 2
13. ልዑልውእቱ 2
14. ሚካኤልአማልደን 2
15. መሰረተ ዜማ 2
16. እንደአናንያ 2
17. ጼናአልባሲሁ 2
18. አባአቡነ 2
19. ገብረመንፈስቅዱስ 3
20. ጊዮርጊስኃያል 3
21. ማኅደረ መለኮት 3
22. ይዌድስዋ 3
23. ያከብርዋ ለሰንበት 3
24. የቀደመ በደላችንን 3
25. አርሴማ ቅድስት 3
26. ከመ ትባርከነ 3
27. ጾም ጸሎታችህንን 3
28. መሓረኒ ድንግል 3

ረጃጅም መዝሙር

1. ሰአሊነቅድስት 3
2. ኃበቀራንዮ 3
3. የአዋጅነጋሪውቃል 4
4. ከክርስቶስፍቅር 4
5. አድርገህልኛልና 4
6. ግነዩ ለ እግዚ አብሄር 4
7. የሥላሴን መንበር 4
8. በምን በምን እንመስላት 5
9. ቤተክርስቲያን ባህረ ጥበባት 5

የንስሀ መዝሙር

1. አንድ ቀን አለ 5
2. ድንግል ሆይ ስላንቺ 5
3. አልተወኝም ጌታ 5
4. ወዳንተ እሰግዳለው 5

5. **አይደለም ምድራዊ 5**
6. **እመቤተማርያም 6**
7. **አቤትየዚያንጊዜ 6**
8. **በጌቴ ሴማኔ 6**
9. **አዛኚቷ አመቤት 7**
10. **እግዚ አብሄር ሆይ እወድሃለው 7**
11. **አድኚኝ እናቴ 7**
12. **እኔስ በምግባሬ 7**

ሚያዚያ 2013 ዓ/ም

1. **ተናገሩ**

   ተናገሩ ድንቅ ስራውንም መስክሩ/2/

   ተአምሩን ለአለም ንገሩ/2/

   ድንቅ ስራውን መስክሩ

   ኖላዊ ትጉኅ ዘኢትነውም /2/

   ማኅበረነ/2/ዕቀብ በሠላም/4/

   የማታንቅላፋ ትጉህ እረኛችን/2/

   ጠብቅልን በሰላም ማህበራችህንን/4/

2. **ኩሎ ዘፈቀደ**

   ኰሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሄር/2/

   በሰማየኒ ወበምድርኒ ወበባህረኒ ወበኩሉ <u>ቀላያት/4/</u>

4. **ንሴብሖ**

   ንሰብሖ/2/ ለእግዚአብሄር/2/

   ስቡሓ ዘተሰብሓ/4/

   እናመስግነው/2/ እግዚአብሄርን/2/

   ምስጉን ነው የተመሰገነ/4/

3. **ኖላዊ ትጉህ**

5. **ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ**

ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ኅበ እግዚአብሄር

እንዘትብል አምላኪየ/2/ ነጽረኒ ወአድኅነኒ/2/

እም ኃይለ ጸላኢ ወፀር

6. **ለጌታዬ ለእግዚአብሄር**

ለጌታዬ ለእግዚአብሄር ስላደረገልኝ ምን አከፍለዋለው/2/

ተመስገን ነው አንጂ/2/ ሌላ ምን እላለው/4/

7. **ስብሃት ለአግዚአብሄር በሰማያት**

ስብሃት ለእግዚአብሄር በሰማያት/2/

ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብ ሃሌሉያ

ሃሌሉያ/3/ ሃሌሃሌሉያ

8. **እንተ በምድር**

እንተ በምድር ስረዊሃ ወበሰማይ አዕፁቂሃ/2/

ሐረገወይን/2/ድንግል ሐረገወይን

9. **በምድራዊ ሕይወት**

በምድራዊ ሕይወት/2/ በፈተና ቦታ

ማርያም ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ/2/

10. **ኢያቄም ወሐና**

ኢያቄም ወሐና እናትአባትሽ

ቤተ አግዚአብሄር ወስደው ስለት የሰጡሽ

መናከ ሰማያት የወረደልሽ

ፍጹም ድንቅ የሆንሽ ማርያም አንቺነሽ/2/

11. **በመኑ**

በመኑ በአምሳለ መኑ አስተማስለኪ/2/

እመቤቴ የእኔ አማላጅ አዛኝቷ

ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ

12. **እመቤታችን ማርያም**

እመቤታችን ማርያም ማኅበራችንን ጠብቂልን በምልጃሽ/2/

ከ መናፍቃን ከከሃድያን ከጠላት ሰይጣን

ሰውረሽ እንድጠብቂን በምልጃሽ/2/

13. **ልዑልውእቱ**

ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር/4/

ሚካኤል/2/ልዑለ መንበር/2/

14. **ሚካኤል አማልደን**

ሚካኤል አማልደን ከአምላካችን/2/

እንዳንጠፋ እንዳንሞት ከአምላካችን/4/

15. መሰረተ ዜማ

መሰረተ ዜማ ወጠነ/2/ ያሬድ ካህን/2/

ያሬድ/3/ ያሬድ ካህን ጥዑመ ልሳን/2/

16. እንደ አናንያ

እንደ አናንያ እንደ አዛርያ

አንደ ሚሳኤል አጽናን አኛን/2/

አጽናን እኛን/2/ አጽናን እኛንም በምነታችን/2/

17. ጴና አልባሲሁ

ጴና ኣልባሲሁ/2/ ለገብረ መንፈስ ቅዱስ

ከመጴና ስሒን

አልባሲሁ ዘሜላት/2/ ዘወረደ ውስተገነት/2/

18. አባ አቡነ

አባአቡነ/2/ መምህርነኣባተክለሃይማኖት/2/

እምአእላፍ ኅሩይ/2/አባ/6/ አቡነ ተክለሃይማኖት/2/

19. ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ገብረ መንፈስቅዱስ ያለም ብርሃን ናቸው/2/

ይኽው ለዘላለም ያበራል ስራቸው/2/

20. ጊዮርጊስ ኃያል

ጊዮርጊስኃያል /2/ መስተጋድል/2/

ገባሬ ተኣምር/2/ ኮከበ ክብር/4/

21. ማኅደረ መለኮት

ማኅደረ መለኮት/2/

ማርያም እመብዙኃን/4/

22. ይቄድስዋ

ይቄድስዋ መላአክት/2/ ለማርያም/2/

በውስተ ውሳጤ መንጦላይተ ወይብልዋ

በሐኪማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ

23. ያከብርዋ ለሰንበት

ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት

ጻድቃን በውስተ ገነት

ወኩሉ ፍጥረት ኣሳት ወኣናብርት

እለ ውስተደይን ያዕረፉ ባቲ

እስመባቲ አዕረፈ እምኩሉ ግብሩ

24. የቀደመ በደላችንን

የቀደመው በደላችህንን/2/ ኣታስብብን/2/

አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን/2/

አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይሁን
ይደረግልን/2/

25.አርሴማ ቅድስት

አርሴማ ቅድስት/2/ ወሰማዕት/2/

ወሰማዕት/5/ አርሴማ ቅድስት/2/

26.ከመ ትባርከነ

ከመትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ/2/

ተዋነይ በጽድቅ/4/ ገብርኤል ሃመልማለ
ወርቅ

27.ጾም ጸሎታችን

ጾም ጸሎታችን ተቀበልልን

ደስ የሚያሰኝ ይሁንልን/2/ኽኽ

እንዳንሸነፍ ኃይልህን ስጠን

አፍሮ ይመለስ ይውደቅ ሰይጣን/2/ኽኽ

28.መሐርኒ ድንግል

መሐረኒ ድንግል ወተሰኃልኒ በበዘመኑ/2/

ለእመ መሓርክኒ/3/ አንቲ ዘይኮንነኒ መኑ

ኮናኔ ሥጋ ወነፍስ/3/ ወልድኪ አኮኑ/2/

ረጃጅም መዝሙር

1. ሰአሊነ ቅድስት

ሰአሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን/2/

አንደ ኤፍሬም እንደ አባታችን

ለምኝልን እመቤታችን

አዝ

ተስፋቸው ነሽና ለፍጥረት ዓለም

እየተመኩብሽ እስከዘላለም

ኃጥያታቸው ተደምስሶላቸው

በአንቺ ጸሎት ዳነች ሕይወታቸው

አዝ

ስምሽም ሥልጡን ነው በእግዚአብሄር
መንበር

ቃልኪዳን ገባልሽ ዓለሙንሊምር

በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ

ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ

አዝ

ዓለም ስታዋጋን በምኞት ስለት

ነፍሳችን ስትዝል ሲከብዳት ኃጢአት

ጨልሞብን ግራ ሲገባን

ብርሃናችን ነይ እናታችን

ኣዝ

የልባችን ጎዘን እጅጉን ከብዶናል

ኃጢታችን በዝቶ መቆም ተስኖናል

እንደ ኤልሳቤጥ እንደዘመድሽ

ደስ አሰኝን ይሰማ ድምጽሽ

2. **ኃበ ቀራንዮ**

ኅበ ቀራንዮ ደብረ መድኃኒት/4/

ቀራንዮ/2/ኅበ ቀራንዮ

የመስቀሉ ቃል ለኛ የ እግዚአብሄር ኃይልነው/4/

ለማያምኑት ሞኝነት ነው ለኛ ግን ሕይወትነው/2/

እንመሰክራለንፈጣሪያችንአለ/4/

እንመነው አንካደው ፈጣሪያችን ቸር ነው/2/

እንመሰክራለን ድንግል እማላጅናት

እንመሰክራለን ማሪያም አማላጅናት

እንመናትአንካዳት የ አምላክ አናት ናት/2/

ኅበ ጥበባት ኃበ ልሳናት/4/

ዩሓንስ/2/ ወንጌለ ስብከት/2/

3. **የአዋጅ ነጋሪው ቃል**

የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበርሃ አየለ

የአግዚኣብሔን መንገድ ኣስተካክሉ እያለ

ምስክርነቱን ዩሃንስ ካስረዳን

ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን

የደናግል መመኪያ የነብያት ገዳም

ዓውደ አመቱን ባርኪልን ድንግልማሪያም

ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና

ካልተስተካከለ መንገድ የለምና

የእግዚኣብሔርን መንገድ አንመስርት ሁላችን

ማለፊያ አንዲሆነን ለመጪው ሀብታችን

አዝ

ክፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ

ጽድቅና ርህራሄ በኛ ላይ ይስፋፋ

ስጋና ደምህን በክብር አግኝተናል

ሕይወት እንዲሆነን አምላክ ተማጽነናል

አዝ

ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን

ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን

ከበደላችንም አንፃን አደራህን

በክፉ እንዳንጠፋ እኛ ባሮችህ

አዝ

4. **ከክርስቶስ ፍቅር**

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው/2/

መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው/2/

አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2/

አግዚአብሄር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለኣለም/2/

በትጋት ተራምደን እንግባ በጠዋት/2/

በደሙ መስርቶ ከሰራልን ቤት/2/

ከቶ የትይገኛል እንዲህ ያለ ቤት/2/

የውሃ ግርግዳ የደም መሰረት/2/

የውሃ ግርግዳ የደም መሰረት/2/

ይኸው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት/2/

5. አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ
አመሰግንሃለው እልል /2/

ለአለመ አለም አማኑኤል እገዛልሃለው
መድሃኒአለም

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ

የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ

ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ

ፈጽሞ አራክልኝ የልቤን ትካዜ

አዝ

አምላኬ ጉልበቴ ኃይለ መመኪያዬ

ጠላት ማሳፈሪያ የ አምነትጋሻዬ

አንደማትተወኝ ኣሁን አውቄአለው

ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለው

አዝ

ትቂቷን አብዝተህ የምትመግብ ጌታ

የምመልስልህ ባላገኝ ስጦት

በቀንም በሌትም ሁሌ የሚያበራ

መንክር ለባህርይ ዕጹብ ያንተ ስራ

አዝ

አምላክ ምስጋና ላንተ ይገባሃል

ለሚስጊኗ ጎጆ በረከት ሰተሃል

ደሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና

ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎል አንደገና

6. ግነዩ ለ እግዚ አብሄር

ግነዩ ለ እግዚኣብሄር እስመ ኄር/2/

አስመ ለአለም ምህረቱ አስመ ለአለም/2/

እናመስግንስህ የኣምላክ እናት
በዝማሬ/2/

የአለም ቤዛ ነውና የማኅፀንሽ ፍሬ/2/

ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ካንቺ ተወልዶ/2/

መለኮት ወረደ ዮርዲያኖስ አኛን
ለመቀደስ/2/

በዩሓንስ እጅ ጠጠመቀ አዳችንን ፋቀ/2/

በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን/2/

በድንግልና የወለድሺው ያንቺው ጽንስ/2/

የድኩማኖች ብርታት ነው የህሙማን
ፈውስ/2/

ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ/2/

በመንግስተ ሰማይ ይኖራል
አንደተከበረ/2/

ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ/2/

ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንች
ነሽ/2/

እመበታችን አናታችን ማሪያም/2/

የተማጽነሽ ይኖራል ለዘለአለም/2/

7. የሥላሴን መንበር

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት

ድንግልን ከመሃል ሚካኤልን ከፊት

አዕላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍራት

እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት/2/

አዝ

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

አያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት

ካህናተ ሰማይ ቅዱስ/3/ሲሉት

ይህንን ልዩ ክብር ሊያዩ የታደሉ

በጽድቅ ስራቸው በምድር ይታያሉ/2/

አዝ

የቅዱሳን ህብረት የቅዱሳን ሃገር

ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር

ጽድቅ አና እርህራሄ የተሞላ ሰማይ

እግዚ አብሄር ያድለን በትንሳኤ እንድናይ

አዝ

8. በምን በምን እንመስላት

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማሪያምን

ምሳሌ የላትም/2/ክብሯን የሚመጥን

አዝ

የሙሴ ጽላት ነሽ የምሕረት ቃል ኪዳን

የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን

የብርሃን መውጫ የኖህ ድንቅ መርከብ

የመላእክት እህት **<u>የሩኅሩኋን ርግብ/2/</u>**

እዝ

የሰለሞን አክሊል የአሮን በትር

የዕዝራ መሰንቆ የጌዎን ፀምር

ድንግል እመቤት ናት የጻድቃኖች በር

ሆና የተገኘች **<u>የአምላክ ማህደር</u>/2/**

አዝ

የቅዱሳን አናት የአለም ንግስት

ችላ ተሸከመች መለኮተ እሳት

ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ

አማልዳ ታስምረን **<u>ከዚህ ኣለም ጣጣ</u> /2/**

አዝ

ከማር ይጣፍጣል የድንግል መሃዛ

አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ

ዓለሙኡ ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና

እናታችን ጽዮን **<u>ይድረስሽ ምስጋና/2/</u>**

9. ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት

ቤተክርስቲያን ባሕረ ጥበባት /2/

አትመረመርም/2/ እጅግ ጥልቅ ናት/2/ ኽኽ

በሥጋዊ ጥበብ ለማወቅ ሲቃጣ

የእምነት መነጸሩን ይዞ ስላልመጣ

አንዳንዱ በክህደት/2/ ፈጣሪውን አጣ/2/

እንመሰክራለን ፈጣሪያችህን አለ

እንመሰክራለን ኣማኑኤል አለ/2/

እንመነው አንካደው አማኔል ቸር ነው

እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት

እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት

እንመናት ኣንካዳት የአምላክ አናት ናት

የንስሀ መዝሙር

1. **አንድ ቀን አለ**

አንድ ቀን አለ የሚያስፈራ

ለጻድቃን የሚያበራ/2/

ጌታ በዚያች ቀን ይመጣል

በግርማ ይቀመታል/2/

አብረው በዚያች ቀን ይመጣሉ

ቅዱሳን መላእክት ሁሉ/2/

የፍርድም አዋጅ ይታወጃል

ነፍስ ሁሉ ይጨነቃል /2/

ኃጥአን ሁሉ ያለቅሳሉ

በግራው ይቆማሉ/2/

ቅዱስ ስሙንም ሰምተው ያመኑ

የፀኑ በኪዳኑ/2/

አብረው በቀኙ ይቆማሉ

ከኃዘን ይሰወራሉ/2/

2. **ድንግል ሆይ ስላንቺ**

ድንግል ሆይ ስላንቺ ነውና መሃሪ

አማልጂኝ ከ አንድ ልጅሽ ከፈጣሪ

ስሙን እንዳልጠራ አንደበትምየለኝ

ፊቱንም እንዳላይ ሥራዬ አሳፈረኝ

ታውቆኛልጥፋቴ ብዙ እንደበደልኩኝ

ትዕዛዙን እንደሻርኩ ሕጉን እንደጣስኩኝ

አዝ

አንተ ክቡር መልአክ ልደቱን አብሳሪ

አማልደኝ ከጌታዬ ለፈጣሪ

በፊቱ እንዳላፍር የተጠራው ለታ

እለምነዋለው ከአሁኑ ይቅርታ

አዝ

ጻድቃን ሰማህታት እናንተ ሁላችሁ

አማልዱኝ ከጌታዬ ከአምላካችሁ

3. **አልተወኝም ጌታ**

አልተወኝም ጌታ ለካስ ይወደኛል/2/

ዛሬም ስበድለው ልጄ ነህ ይለኛል

ዛሬም ስበድለው ልጄ ነሽ ይለኛል

አዝ

በበደል ጉራንጉር በኃጥያት ጫካ

ብጠፋበት እንኳን ኣልተወኝም ለካ

ዛሬም ልጄ ብሎ ዳግም ይጠራኛል

ለካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል

ኣዝ

ለስልጣን ለክብር ብዬ ስክደው

ለገንዘብ አድልቼ አኔ ብረሳው

ለእኔ ያለው ፍቅር አልቀነሰብኝም

ዛረም ይወደኛል ጌታ አልጠላኝም

አዝ

ታዲያ ለዚህ ፍቅሩ ለሌለው ወሰን

ከጭንጫ መቃብር ላወጣኝ እኔን

በሕይወት ሁሉ ፍጹም ለመራኝ

ክብርና ምስጋና አቀርባለሁኝ

4. ወዳንተ እሰግዳለው

ወዳንተእሰግዳለው ሳለው በሕይወቴ

ላንተም እሰግዳለው እስከ ለተሞቴ

አንተ ነህና መድኃኒቴ የዘላለም ቤቴ/2/

ሳይመሸብኝ ቀኑ ሳይጨልም ድንገት

በጽድቅህ ጎዳና ልጓዝ ወደፊት

ምራኝ መንገዱን አሳየኝ እንዳልሳሳት/2/

የነፍስ የስራዬ የሕይወቴ ቤዛ

አትበለኝ ችላ በደሌ ቢበዛ

አንተን አምጄ እኖራለው ወዴት እሄዳለው

አንተን አምጄ እኖራለው ወዴት እደርሳለው

5. አይደለም ምድራዊ

ይህ ቁርባን ክቡር ነው ፍፁም ሰማያዊ/2/

እንዳይመስለን ተራ አይደለም ምድራዊ/2/

አምላካችን ሆይ አንተ ይቅር ባይ

አንደቸርነትህ በደልን አትይ/2/

አሜን አሜን ብለን ተቀብለናል

በድፍረትም ሳይሆን በፍራት ቀርበናል/2/

አዝ

ማክበር ይገባናል በትኅትና ሆነን

ደፍረን ኣናቅለው እንዳያቃጥለን/2/

እንደምታዩት ይህ ቁርባን ፈራጅ ነው

እንደሌላው ሳይሆን የተቀደሰነው/2/

አዝ

ሱራፌል ኪሩቤል ጸወርተ መንበር

ለመያዝ ያልቻሉት ፈርተውት በክብር/2/

አኛም ተመገብነው ኣገኘን ድህነት

ለነፍስ ለስጋችን ሆነልን ሕይወት/2/

6. እመቤተ ማርያም

እመቤተ ማርያም እለምንሻለው

በለቅሶ በዋይታ ፊትሽ ወድቀአለሁ

እመቤቴ ስሚኝ እለምንሻለው/2/

ኃዘነን ጭንቀቴን ለማን እነግራለው

ችግሬን ጉዳቴን ለማን ኣዋያለው

እመቤቴ ስሚኝ ተማጽኜሻለው/2/

ኃዘኑ በዛብኝ ፈተናው ከበደኝ

እንደምን ልቻለው አኔስ ደካማነኝ

የአማኑኤል እናት ፈጥነሽ ድረሺልኝ/2/

በጣም ተንገዳገድኩ ልወድቅ ነው እኔ

አመ ኣምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጎኔ

ምንም ኣጋር የለኝ ካንቺ በቀር ለኔ/2/

7. አቤት የዚያን ጊዜ

አቤትየዚያንጊዜክርስቶስሲመጣ

ትንሹምትልቁም /3/ መድረሻውንሲያጣ

ከምስራቅከምዕራብከሰሜንከደቡብ

ነፋሳትሲላኩ/2/ መዓትንለማዝነብ

ሰማይናምድርባንድሲዋሃዱ

የትይሆንመድረሻው/3/ የትይሆንመንገዱ

አዝ

ጻድቃን በቀኝ በኩልአጥዓን በግራ

ሲነፋ መለከት/3/ ሲደለቅእንዚራ

ምድር ቀውጢ ስትሆን አጽም ሲሰበሰብ

ኃፍረት ይይዘዋል/3/ሰው ለፍርድ ሲቀርብ

አዝ

ጩኽት ሲበረታ የማይጠቅምለቅሶ/2/

አንደ ቁራ ጠቁሮ/3/ ፅልመትንተላብሶ

ገነትን ሲያገኙ ጻድቃን በስራቸው

ኃጣን ወደሲኦል/3/ ተፈረደባቸው

አዝ

8. በጌቴ ሴማኔ

በጌቴ ሴማኒ ባታክልቱ ቦታ/2/

ለኛ ሲል ጌታችንባለም ተንገላታ/2/

አዳም ና ሄዋን ባጠፉት ጥፋት/2/

ለኛም ነበረብን የዘላለም ሞት/2/

መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ/2/

ይገርፉት ነበረ አይሁድ በየተራ/2/

ድንግል ኣልቻለችም እምባዋን ልትገታ/2/

እያየች በመስቀል ልጇሲንገላታ/2/

በአምላክነቱ ሳይፈርድባችው/2/

አንዲህ ሲል ጸለየ አባትሆይ ማራቸው/2/

በረቂቅ ሥልጣኑ ሁሉን የፈጠረ/2/

በሰዎች ተገርፎ ሞቶ ተቀበረ/2/

ፍቅሩን የገለጸው ተወልዶ በስጋ/2/

ኢየሱስ ጌታ ነው አልፋ ና ኦሜጋ/2/

9. አዛኚቷ አመቤት

አዛኚቷ አመቤት አትርሺኝ

የፈጣሪዬ እናት ኣስታውሺኝ

በምህረትሽ/3/ተማለጂኝ

የመከራ ነፋስ አጠቃኝ

ሕይወቴ ዝላለች ደከመኝ

ከጥላሽ ስር/3/ አሳርፊኝ

አዝ

ከችንቀት ባህር ውስጥ አድኚኝ

ፈጥኜ ሳልጠፋ አስጥዪኝ

እመቤቴ/3/ ተመልከቺኝ

አዝ

አምላኬን ለማየት አልችልም

ኃጥያቴ ብዙ ነው አይሆንም

ካልደገፍሺኝ/3/ እኔ አልድንም

አዝ

ድንግል እመቤቴ እባክሽ

ከፈጣሪ አስጣርቂኝ ከልጅሽ

ያላንቺ ማን/2/ ያላንቺ ማን አለኝ አስታዋሽ

10.እግዚ አብሄር ሆይ እወድሃለው

እግዚ አብሄር ሆይ እወድሃለው

ስለስምህ እዘምራለው

ፍቅርህ እኔን ያበረታኛል

እንደ እግዚ አብሔር ከየት ይገኛል

አዝ

ዓለም ሁሉ በጠላኝ ጊዜ

ስንገላታ ይዞኝ ትካዜ

አንተ ከኔ አልተለየህም

እግዚ አብሔር ሆይ ወደር የለህም

አዝ

ሞቷል ብለው ቀብረውኝ ሰዎች
ምስኪን ሆኜ ሳይኖረኝ አንዳች

ከመቃብር ቆፍሮ አወጣኝ

አይዞህ ብሎ አምላኬ አጽናናኝ

11.አድኚኝ እናቴ

አድኚኝ እናቴ ከስጋ ፈተና

ስጋዬ ከሃጢያት ከቶ አልራቀምና

ሸክሜ የከበደ ብቸኛ ሆኛለው

አትለዪኝ ድንግል አደራ እልሻለው/2/

አዝ

የአማኑኤል እናት የተዋህዶ አክሊል

አትጥፊ ከመሃል እንድቶኚኝ ኃይል

ምንም ቢበዛብሽ የኛ ጉስቁልና

ከኛ ጋራ ከሆንሽ አለን ቅድስና/2/

አዝ

ተስፋዬ ነሽና እመካብሻለው

ግራ ቀኝ አልልም ምርኮኛሽ ሆኛለው

ስቅበዘበዝ አይቶ ተስፋ የሰጠኝ

እግዚ አብሄር ይመስገን ካንቺ ያስጠጋኝ/2/

አዝ

በስጋ ደክሜ በነፍሴ እንዳልጠፋ

እማጸንሻለው ድንግል የኔ ተስፋ

የመንግስቱ ወራሽ እንድሆን አድርጊኝ

መልካም ስራን መስራት አኔን አስተምሪኝ/2/

አዝ

አንቺ የለለሺበት ጉባኤው ባዶ ነው

በቁም የደረቀ ህይወት የተለየው

በመካከል ገብተሽ ሙይ የጎደለውን

ሠርጉ ተደግሷል ጎብኚልን ጓዳውን

አዝ

12. እኔስ በምግባሬ

እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለው

እዘኚልኝ ድንግል እለምንሻለው/2/

ያንን የሳት ባህር አንዳላይ ኣደራ

ድረሺልኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ

የዳዊት መሰንቆ የኤሊያስ መና

የናሆም መድኃኒት ነይ በደመና/2/

አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ

የልቤ መጽናኛ እረዳት ምርኩዜ

አፈሳለው እምባ በጣም ተጨንቄ

እማጸንሻለው በደሌን አውቄ